፫ THE Addis Ababa Conference:
The Implication for Inter-African Cooperation in Education. 1961-1979
A Dissertation Universiity of
Oklahoma College
By Gashaw Weyneshet Lake 1981

## ረቂቅ ሀሳቡ ባጭሩ

እ.ኤ.አ. በግንቦት ወር 1960 ዓ/ም በአዲስ አበባ ለአሥር ቀናት የተከሄደው የመጀመሪያው «የአዲስ አበባው ጉባኤ» በመባል የታወቀው ስብሰባ ከዚያን ዓመት ጀምሮ ለሚቀጥሉት 20 ዓመታት እንዴትና ምን ያክል በአፍሪካ አገሮች መከከል ያለውን መተባበር እንደረዳ የሚተች ጽሑፍ ነው።

እ.ኤ.አ. በ1960ዎቹ ዓመቶች ውስጥ አያሌ የአፍሪቃ ሀገሮች ከቅኝ ግዛት ነፃ በወጡበት ጊዜ እያንዳንዱን ሀገር የብሔራዊ ደህንነት፣ የኢኮኖሚ መደሰደል፣ እንዲሁም ባጭር ጊዜ ውስጥ ዘመናዊነትን የመቀዳጀት ችግሮች ተደቅነውበት ነበር። እነዚህን አበይት ችግሮች ለመወጣት ከተዘየዱት ዘዴዎች መከከል አንዱና ዋነኛው ትምህርት ነበር። ከዚህ ውሳኔ በኋላ ትምህርትን በየሀገሩ በወል ለማሰራጨትና ለማስፋፋት የጋራ መገናኛ ይሆን ዘንድ ጉባኤ መመሥረት አስፈላጊ ሆኖ በማግኘታቸው «ትምህርትን በአፍሪቃ ለማደራጀት የአፍሪቃ ሀገሮች ጉባኤ» ወይንም ባጭሩ «የአዲስ አበባ ጉባኤ» የተሰኘውን መድረክ ፈጠሩ። የዚህ ጉባኤ መፈጠር በትምህርት አኳያ ያሉትን ችግሮች ለማስወገድ በሚደረገው ጥረት የመጀመሪያው ሲሆን በአፍሪቃ አህጉር ደረጃ የተተለመ በመሆኑ ደግመኛ ጥቅም ነበረው።

ይህ ጥናት የመረመራቸው ነጥቦች፤

፩ የአፍሪቃ ሀገሮች ይህን ጉባኤ ሲቆረቆሩ የተነሡበት መነሻ ምክንያት ምን ነበር?
፪ ይህ ጉባኤ ትምህርትን አስመልክቶ መሠረታዊ ፍልስፍናው ምን ነበር?
፫ ጉባኤው ይህን ፍልስፍና በያንዳንዱ ሀገር ግብር ላይ መዋሉን ለማረጋገጥ የተጠቀመባቸው ዘዴዎች ምን ነበሩ?

ጥናት ከዚህ ቀደም የኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴን ታሪካዊ ሂደት የገመገሙትን ጽሑፎች በመመርመር ያሳቸውን ድክመት በተለይም በአመለካከት ደረጃ ዝግና ቀኖናዊ (dogmatic) የሆኑትን በመቃረን ትክክለኛውን ሀቲታዊ (dialectical) አቀራረብ ለማሳየት ይሞክራል። ስለዚህም ጥናቱ ሀቲታዊ ንድፈ-ሀሳብን (Dialectical Theory) በመጠቀም የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ በ15 ዓመታት ውስጥ ያጠናቀቃቸውን ፖለቲካዊ ቁም ነገሮች ይገመግማል። ማዕከላዊና አቢይ መከራከሪያው ሰይ በተመለከተው የጊዜ ወሰን ውስጥ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ዲሞክራሲ ስላልነበረና ፖለቲካዊ ነፃነቶች የተነፈጉበት ወቅት ስለነበረ የተማሪው እንቅስቃሴ የፖለቲካ ፓርቲ ጠባይ ይዞ በማዕከላዊው መንግሥት ላይ የተቃውሞ ፖለቲካውን መርቷል የሚል ነው።

ጥናቱ ስድስት ምዕራፎችን ይዟል፤

፩ ይህ ክፍል መንደርደሪያ ሀሳቦችና ለጥናቱ መጠቀሚያ የሆነውን ንድፈ-ሀሳብ እንዲሁም ለጥናቱ መነሻ የሆኑትን ስለተማሪ ማህበር በተለይም ስለኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ የተፃፉ መጽሐፍትንና ጽሑፎችን ይገመግማል።

፪ ይህ ክፍል የተማሪው እንቅስቃሴ በተከሄደባቸው ዓመታት የነበረውን የሕብረተሰቡን ፖለቲካ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ በተለይም በከተሞች የነበረውን የመደቦች አሠላለፍ ይገመግማል።

፫ ይህ ክፍል በውጭ ሀገሮችና በሀገር ውስጥ የነበሩትን የተማሪ ማህበሮች አነሣሥ ታሪክ ባጭሩ ይተርካል። የዚህ ምዕራፍ አቢይ ተግባር የውጭው የኢትዮጵያውያን ተማሪዎች እንቅስቃሴ እከል ከውስጡ እንቅስቃሴ እንዴት እንደተዘመደና እንደተሣሠረ ማሳየት ነው። ስለዚህ ይህ ክፍል በተለይ የተማሪው እንቅስቃሴ በድርጅት አወቃቀር ተግባሩ ላይ ምን ተግባሮች እንደፈፀመ አጉልቶ ለማሳየት የሚሞክር ነው።

፬ ይህ ክፍል የተማሪው እንቅስቃሴ ያደረገውን ተግባራዊ የፖለቲካ እንቀስቃሴ ይተርካል። በዚህ ምዕራፍ ላይ ጎልቶ የሚታየው በሀገር ውስጥ የነበረው የተማሪ እንቅስቃሴ አካል ሚና ነው።

፭ ይህ ክፍል ደግሞ በተማሪው እንቅስቃሴ ውስጥ የተካሄዱትን የፖለቲካ/ንድፈ-ሀሳብ ክርክሮችና ጉባኤዎች ፤ እንዲሁም የወጡትን የፖለቲካ ውሳኔዎች ከነሂደቱ ለማሣየት ይሞክራል። ይህ ተግባር በተለይ እንፃራዊ የፖለቲካ ነፃነት ባለበት ከኢትዮጵያ ውጭ ባሉ ሀገሮች ውስጥ የተማሪው

እንቅስቃሴ አካል ያደረገውን አስዋጽዖ ይመለከታል። በተማሪዎች መካከል የነበሩት ፖለቲካዊ ትግሎች ላይ ትኩረት በሚሠጥበት ጊዜ ምን ያክል ጥልቀት ያለው ውይይት ማድረግ እንደቻሉና ከሌላው የኢትዮጵያ ሕብረተሰብ ለየት ያለ ፖለቲካዊ ጠባይ እንዲስያዛቸው ለማሳየት ሙከራ ያደርጋል።

፯ መደምደሚያው ክፍል በመጀመሪያው በተማሪው እንቅስቃሴ ላይ የተጻፉትን ሂሶች ጽሑፍ በመመርመር ሂስ ያቀርብና መከራከሪያ ነጥቡን ለማስመር የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ ያከሄዳቸውን ድርጊቶችና ሂደቶችን በማገናዘብ ይደመድማል።

* * * *

## የሚቀጥለው ጥናታዊ እትም፤

## ድርቅና ጠኔ በኢትዮጵያ

፪ኛ ዓመት ቁጥር ፫ ድርቅና ጠኔ በኢትዮጵያ በሚል ርዕስ ጥናታዊ ቁጥር ይዞ እንደሚወጣ ማስታወቃችን ይታወሳል። ይህ ቁጥር በኢትዮጵያ ላይ በተደጋጋሚ የሚመጣው የድርቅ ችግር ላይ መሠረታዊ ጥያቄዎችን የሚመልስ እንደሚሆን ተስፋችን ነው። ጥያቄዎች ላይ መልስ በሚሠጥበት ጊዜ የአንዳንድ ቃላት ፍች አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ደራሲው ቃላቱን ወይንም ጽንሰ-ሀሳቡን በማብራራት እንዲጀምር እናስታውሳለን።

በኛ በኩል ድርቅ ብለን የምንጠራው በፀሐይ መበርታት ምክንያት መሬት ላይ ያሉ እጽዋት መድረቅ የሚገደዱበትን ሁኔታ ለመግለጽ ነው። ብዙውን ጊዜ ድርቅ ከዝናም መቋረጥ ወይንም መጥፋት ጋር ይዛመዳል።

ጠኔ ብለን የምንጠራው ደግሞ ከረሀብ ደረጃ አልፎ ሕዝቡ የሚበላው ምግብ የሚጠጣው ውሃ ተራግፎ ሕዝቡ በግፍ የሚሰደድበትና የሚሞትበትን ደረጃ ለመግለጽ ነው።

ድርቅና ጠኔ በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ሲመረመርለድርቅ ተፈጥሮአዊ መነሻ ምክንያት ቢኖርም ከተራ ረሀብ ማዶ ሕዝቡን ሠፈሩንና ቀየውን ለቆ መሰደድ የሚገደድበት እና በገፍ የሚሞትበት ሁኔታ በምን ተጨማሪ ምክንያቶች እንደሚፈጠር ለማወቅ ጭምር መሆን ይኖርበታል። ስለዚህም ድርቅ፣ ረሀብና ጠኔ ከሀገሪቱ ኢኮኖሚ፣ ከፖለቲካ፣ ከሕዝብ ባህል፣ ከዓለም አቀፍ የአየር ጠባይ ከፍልስፍና ከታሪክ እና ከመሳሰሉት አንፃር እየታየ ቢተነተን ሰፊ ዕውቀታዊ ክምችት ሊፈጥር ይችላል። ድርቅ ሀገሪቱን ከመታ በኋላ የድርቅ እስቸኳይ አስተዳደር የሚያሻው በመሆኑ በኢትዮጵያና በሌሎችም ሀገሮች የድርቅ አስተዳደር ምን እንደሚመስልና እንዴትስ መሻሻል እንዳለበት መጠቆም ወደፊት ለሚመጡት ችግሮች እስቸኳይ

መፍትሄ ለመዘየድ ይረዳል።

ቀጥሎም የድርቅና ጠኔ ችግር እንዴት ሊወገድ ይችላል የሚለው ጥያቄ ከመነሻ ምክንያቱ በመነሳትና ከርሱም ጋር በማዛመድ መፍትሄ መጠቆም ሌላው ተግባር ነው። አንዳንድ ደራሲያን በአንድ ድርቅ በጠቃው ሀገር ውስጥ በማንኛውም ጊዜ በቂ የምግብ ክምችት ይኖራል ይላሉ። ችግሩ ያለው የምግቡን ክምችት በድርቅ ለተጠቃው ሕዝብ ማዳረሱ ላይ ነው ይላሉ። ሌሎች ተከራካሪዎች ደግሞ፤ ምንም እንኳ ምግብ ቢኖር በመደብ ልዩነት የተነሣ የእህል ዋጋ ስለሚንርበት ደሀው ክፍል ገዝቶ ሕይወቱን ማቆየት ይሳነዋል ስለዚህም የመሞት ወይንም በበሽታ የመበከል ዕድል ይጠብቀዋል ይላሉ። ሌሎች ተከራካሪዎች ደግሞ የጠኔ ችግር ከመደብ አሰላለፍ ጋር የተቆራኘ ስለሆነ ሥርዐታዊ ለውጥ የግድ አስፈላጊ ነው ይላሉ። ሌሎችም ክርክሮች ይኖራሉ።

ከአዘጋጆው ክፍል

## ለ «እዋልደ-ወንዴ»

# መነሻ

አንድ ኅብረተ ሰብ ባላሰበውና ባልጠበቀው ዓይነት፣ ከአንድ መራራ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና፣ የሶሻል ቀውስና ክስ ረት ውስጥ ድንገት በተዘፈቀ ጊዜ፣ በግለሰቦችም ሆነ በማኅበረ ሰቡ ላይ ብዙ አሳዛኝና አስቀያሚ ድርጊቶች ይፈጸማሉ። በመ ንታ ትውልዶች ያስተሰሰብ ግጭት አንጻር፣ ወላጅን ከተወ ላጅ፣ ወንድምን ከወንድም፣ ወንድን ከሴት፣ ከተሜን ከገ ጠሬ፣ በአእምሮ አዳሪውን ከጉልበት አዳሪው፣ ........ ያጋ ጫል፣ ያናቁራል፣ ያናችፋል። ይህ ዓይነቱ ሁኔታ፣ አንድ ዓይነት ማኅበረ ሰብ ፣ በነባር የለውጥ ሕግ ተገድዶ፣ ወደ አዲስ ማኅበረ-ሰብነት ሲለወጥ የሚያጋጥም፣ የሰው ልጆች በሚኖሩበት አካባቢ ሁሉ፣ ሲመጣ ሲሔድ፣ ሲወጣ ሲገባ፣ ሲያረጅ ሲተካ፣ ሲዘቅጥ ሲለወጥ፣ በየዘመኑና በየወቅቱ የሚ ከናወን ቀዋሚ ክስተት ነው።

የለውጡን ሁኔታና ኪደት፣ ይዘትና ቅርፅ፣ የሚወ ስኑት ምክንያቶች፣ አካባቢና ዘመን፣ የማኅበረሰቡ የንቃት ደረ ጃና ያደረጃጀት መዋቅር፣ የትዝምደ-ምርትና እምጻኤ -ምርት፣.... ዓይነተኞቹ ሲሆኑ፣ ያለፈው ትውልድ ያስተሳሰብ ቅርስና ይጠቀምበት የነበረው የታዳጊ ሕዋናት ያስተዳደግ ሥርዓት በየበኩላቸው ለሚፈጠረው ለውጥ አስተዋፅኦ አላቸው። ያን ዘመነ-ማዕዶት ( የሽግግር ዘመን) በሚገባ ለማስ ተናገድ ያልተዘጋጀ ሕዝብ፣ አቤት የሚደርስበት ፍዳ!

በዚች ቍንጽል ታሪክ ውስጥ ይህ እውነታ ከድሕረ የካቲት ወዲህ በሰፈው ማኅበረ-ሰብ ውስጥ ቀርቶ፣ በትንሽዋ አንድ ቤተ-ሰብ ውስጥ እንኳ፣ እንዴት እንደተንጸባረቀ ያሳ

ያል። የወንድማማቾቹና የወላጆቻቸው ታሪክ የነበረና ያለ እውነታም እንኳ ቢሆንም፣ ጭብጣዊ የታሪኩ ይዘት በሕይወት ያሉ ሕያዋንን ጭምር በተምሳሌት ከመጠቀሙ በስተቀር፣ ማንንም አይመለከትም። በሥነ-ጽሑፍ ታሪካዊ ኪደት ውስጥ፣ ብዙ ጊዜ ተዘውትሮ እንደታየው፣ አንዱ ደራሲ ካምቻትካ ተቀምጦ የጻፈው ድርሰት፣ ከነሙሉ ባሕርያቱ ጋር ሌላ ደራሲ አላስካ ተቀምጦ ከጻፈው ታሪካዊ ይዘት ጋር ያለ ነገር አባትና ያለ ጥሎሽ፣ ያለ አማጭና ረማጭ ተጋብቶ ይገ ኛል። ፈረንጆቹ ይህን መሰል አጋጣሚ "ኮኢንስደንስ" ይሉታል። "ተአምራዊ ጥምረት ወይም ሳይገናኙና ሳይተያዩ ተመሳስሎ በመስተጻምርነት መዋሐድ" እንደማለት ነው። እንደዚህም ሁሉ በዚህ ቀንጽል ድርሳን ውስጥ ሰፍረው የሚገኙ ባሕርያት በሙሉ የኮኢንሲደንስ አጋጣሚ ካልሆነ በስ ተቀር፣ "እኔን ይሆናል" የሚለውን ባይ ሁሉ በጭራሽ አይመለከትም። የኢትዮጵያ ድሕረ-የካቲት ኩዴኩዶ ካስወለደው የቀውስ ዱብ ዕዳዎች ውስጥ አንዱ ክሥተት እንደሆነ ግን ሁላችንም እንደምንገነዘበው አምናለሁ። ያንድ ቤተሰብ ልጆች የርስ በርስ መከሳከስ፣ የወላጆቻቸውን ጤንነት እንዳቃወሰው፣ በዚህች አጭር ታሪክ አማካይነት ለማሳየት መሞከሬ፣ የደረሰብን ቀውስና ክስረት ምን ያህል የሚጐመዝዝ መራራ ሡፍነግ መሆኑን እንደሚያስረዳልኝ ተስፋ አደርጋለሁ። ከዚህ አስተሳሰብ ክልል ውጭ ግን የሚሠነዘር ሌላ ትርጉም ቢኖር፣ ትርጁማኑን እንጅ እኔን አይመለከትም።

# «እዋልደ-ወንዴ»

ገ. ኑ. ብልጣሰር
(ስዊድን)

«. . . መከረኛ እናት መንታ ልጆቹ ወልዳ፣
እንዴ ሳት ሴሳው ማይ፣ ጽሩራን ዱብ ዕዳ፣
ወግ ደርሷት ሳትሮር፣ በልሠራቸው ፍዳ፣
ሳትኖር ልትሞት ነው፣ ህይወት ሆኗት ባዳ . . .»

. . . ያለችበት ማኅበረ ሰብ ያወጣለት ስያሜ «እናት» ነው። እንስፍስፏ እናት፣እምዬ። ስምነቱ የወል፣ ስም ይሁን እንጅ የትኛዋም እናት እንደ ግል የተፀውኦ ስሟ ታየዋለች። ስምነቱ የመጀመሪያዋ ሴት በወላጅነት እስከታወቀችበት ወቅት አለ፣ ይኖራልም። በዘመናት መከከል ሲንፏፏ የሚኖረውን የትውልድ ዝማ ያስገኘችና የምታስገኝ ምንጭ በመሆኗ፣ በየትኛውም ሕዝብ፣ በማናቸውም ሀገር እንደተከበረች ትኖራለች። ለፈፀመችው የተፈጥሮ ሞያዋ ይህ የክብር ስጦታ ቢያንሳት እንጂ አይበዛባትም። ለዚህም ውለታዋ በሕይወቷ እስካለች ድረስ በሰላም፣ በደስታ፣ በምቾት፣ ለመኖር ሌላው እንኳ ቢቀር የማህፀኗ ፍሬዎች ከሆኑት ልጆቿ የምትጠብቀው ተራ ወሮታ ነው።

በምንኖርበት ሥርዓተ በሕርይ ድክመት የተነሳ ብዙዎች ነገሮች እንደሚጠበቁት ሆነው አይገኙም። በዚህ ላይ ደግሞ የጥቂቶች ሰዎች የግብዝነት ጠባይ ሲበረዝበት የባሰውን መራራ ሁኔታዎችን ያስያሉ። በዘመናችን እንዲህ ያሉ ጉምዝዝ ድርጊቶች፣ ከመቸውም ጊዜ ይልቅ ጉልተው ይገኛሉ።

እንደሚታመንበት ሁሉ፣ ሕገ-ተፈጥሮ የራሱ መመሪያዎች አሉት። በዚህም መሠረት ፀሐያችን ሙቀቷዋንና ፀዳሏን ከመስጠት አልተቆጠበችም። በዚህም ዕለታት ይነጋሉ ይመሸሉ። ዕጽዋት ያብባሉ ያፈራሉ። ክረምትና በጋ ይፈራረቃሉ፤ ንፋበት በዘፈቀደ

አይነፍሱም። የመንገደ ምዕራብ ሥምሪቱ፣ የራሱ ሕገ-አመክንዮ አለው። የሥግረቱ መፍጠንና መዘግየት የራሱ የሆነ መርሖ አለው። ማያት ይፈስሰሉ። ከልተገደዱ በስተቀር ፍሰታቸው የተዋረደ ቀልቀሊት ነው። ከኽረት በላይ የሚጠጣን ጅብ፣ ከበታቹ የምትጠጣውን እህያ አደፈረሰችብኝ ማለት አይችልም። ...ዓለም ከነተፈጥሮዎቿ በጤነኛ ኪደት ለይ ትገኛለች። የሚያንገዳግዷት እንከኖቿ ግን.ጥቂት አይደሉም። አመንጭዎችም ኢሰዎች ናቸው!!

ከሚኖሩበት ደመ ነፍስ ፍጡራን ሁሉ፣ ሰው የተባለው፣ ዓለምን እንደነጀሰት አለ። የሚበላውን ከሚ ኩሳባትና የሚጠጣውንም ከሚሸናበት አልፎ፣ በሠራው መርዙ እየመረዘት ነው። የነስነሰባት መርዝም፣ ሲጠዘጥዘትና ሲመዘምዘት ቆይቷል። የሰዎች ዓለምን መድፈርና ማስቸገር፣ ከራሳቸው የርሰበርስ ግጭት የተፈጠረ ነው። ፍልስፍናቸው እርስ በርስ ይፋጫል። አንዱ ክፍል የሰዎች መሠረት ግለሰብ ነው ብሎ ሲያስተምር፣ ሌላው ደግሞ ቤተ ሰብ ነው እያለ ያስተምራል። የቀረው ክፍል ደግሞ፣ ጠቅለለው ኅብረተሰብ ነው ብሎ ይሰብካል። በዚህ በተሣከረ እስተሰሰብ ውስጥ፣ ሙሌዎች ይጠቀማሉ፣ የዋሁን ይጉዳሉ። የመንታ ጽንፍ አበሎች በተቆራቆሱ መጠን፣ ዳፋቸውና ጦሳቸው ሌላውን ገር ክፍል እንደረበሸ ነው። ጽንፋውያን ግን፣ ምንጊዜም «ፐሪንሲፐል ያድናል፣ ፐሪንሲፐል ይገሳል» ይሳሉ። የነሱ ዓላማ ግብ እስከመታ ድረስ፣ ዓለም የሆነችውን ብትሆን፣ ደንታ የላቸውም። የነሱ ምኞት ይፈፀም እንጅ፣ አረጋውያን ወለጆቻቸው፣ የዋሁ ሕዝባቸው ጤዛ ቢለብስ፣ አፈር ቢምስ ደንታቸው አይደለም። የነሱ የራሳቸው ሐሳብ ብቻ የነጠረ የጠራ ይመስላቸዋል። የሌላውን፣ በፈለገው ዐይነት በቂ አሳማኝ ማስረጃ ቢቀርብም ይሞታሉ እንጅ አይቀበሉም። ይህ ግትርነታቸው የገመዱት ይመስል እየከረረ ይወጥራል። ጦዘ በሚወጠርበት ደረጃ ሲደርስ፣ ዐይነ ኅሊናቸው ጨርሶ ይታወራል። በዚያን ወቅት የሚሠሩት ሁሉ አይታወቃቸውም። የሚፈስ የሰው ደም፣ ተራ ውሃ ይመስላቸዋል።

ለእንደዚህ ያሉ ልጆች እናት የሆኑ አንድ እመቤት አዲስ አበባ

ይኖራሉ። ስማቸውም ወ/ሮ ትምክህተ ይባላል። ተጀምሮ እስከሚጨረስ ያዲስ አበባ ነዋሪ ናቸው። ወ/ሮ ትምክህተ በኖሩበት ማኅበረ ሰብ ሥርዓት መሠረት እኩያቸውን በቁርበን ተድረው ረዥም ጊዜ ኑረዋል። በሕግ ተፈጥሮ ሥርዓትም ልጆች ወልደው አሰድገዋል። በለቤታቸው ባለምባራስ ወንዴ ይባላሉ። በዕድሜ ከወ/ሮ ትምክህተ ጋር ብዙ አይበላለጡም። ንብረታቸው የደራ ትዳራቸው የሞቀ ነበር። በዚያ የረዥም ዘመን የትዳር ዘመናቸው፣ አንድ ጊዜ ብቻ መንታ ወንዶች ወልደው ነበር። ይህም የሆነው የጣሊያን ወረራ ከከተመ በኋላ ነው። በስለት ኋላ የተገኙ ልጆች ነበሩ። «ወንዴ ወንድ ወለደ» የሚል ዘፈን አስፈልስፈው ወራት አዘፍነዋል።

እሊህ መንታ ልጆቻቸው፣ ለወ/ሮ ትምክህተና ባለምባራስ ወንዴ የሕይወታቸውን ያህል፣ ምትክ የማይገኝላቸው ቅርሶቸው ነበሩ። የአከባቢያቸው ሥልጣኔና ባሕል የፈቀደላቸውን ያህል፣ በሚገባ አሰድገዋቸዋል። እጅግ ስለሚሰሱላቸውም፣ አንዳንዴ በጣም ያሞለቅቋቸው ነበር። በተለይም፣ የማቆለመጫ ስም ሰጥተው ከዋና ስማቸው ይልቅ፣ በዚሁ ስማቸው እንዲጠሩ አርገዋል። እንደ ውልደታቸው ቅደም ተከተል «መሩ» እና «መራ» ይባሉ ነበር። ትምህርት ቤት ውለው እስኪመጡ ድረስ፣ ወለጆቻቸው ልባቸው ተሠቅሎ ይውላል። ተጨንቀው ተጠበው ነው ያሰደጏቸው። ጉንፋን እንኳ ሲይዛቸው፣ ከልጆቻቸው ይልቅ ራሳቸው ይታመሙ ነበር። ይሰሱላቸው የነበሩ መንታ ልጆቻቸውም ቢሆኑ በትምህርቱ አልሠነፉም ነበር። እንዲያውም አይተኙበት ጀንዲ ሆነ እንጅ ዲግሪ እስከማግኘት ደርሰዋል። በዚህም ሙያቸው ተሸመውበታል፣ ተሸልመውበታል።

«ልጆቼ» እያሉ ወለጆ ወ/ሮ ትምክህተና ባለምበራስ ወንዴ ጥሩ ኑሮ በጀመሩበት በተደላደለ ሕይወት ውስጥ፣ ያልጠበቁት ነገር ድንገት ፈነዳ። የየከቲቱ ሕዝባዊ ግፊት ያመጣው ዱብ ዕዳ ነበር። አደዲስች ሁኔታዎች መጡ፣ አዳዲሰች ሁኔታዎች ሔዱ። ነገሮች ተመሠቃቀሉ፣ ተሠበጣጠሩም። መከሩን ከእንክርዳድ የሚለየው

ሰፈድና ወንፊት ሳይቀር፣ በቀጥቃጭ መራጃ ተተክቶ፣ የማይደረገው ተደረገ። ንጹሐን ያለፍዳቸው ወደቁ። ግለሰቡ በየምርጫው ወገነ። በዚህም ድርጊት ላይ መንታዎቹም፣ መሩ እና መራ ነበሩበት። የሚደንቀው፣ አሠለሰፋቸው ጉራ ለይቶ መሆኑ ነበር። ከርበ ዓመት በላይ በፍቅር ተሣሰረው የነበሩ መንቶች፣ የለየላቸው ጠላቶች ሆኑ። አንዱ የማዕከላዊ መንግሥት ተጠሪ ሹም ሲሆን፣ ሌላው ፀረ ማዕከላዊ መንግሥት ሆኖ ተሠለፈ። በየከምፓቸው መሽገው፣ «ቆይ ባላርድህ» በመባባል ይፎክከሩ ገቡ። ይህን ሁኔታ በስተኋላ ላይ የተረዱ ወላጆቻቸው፣ መግቢያ ቀዳዳ፣ መሸሸጊያ ጎዳ፣ መሮጫ ሜዳ ጠፋባቸው። የሚሆኑትን አጡ። የሚመገቡት እስኪያስመልሳቸው ድረስ፣ የመንፈስ ሕመም ተጠናወታቸው። ደረቅ ጭንቀት! የልጆቻቸው እንዲያ መሆን «በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ» እንዲሉ እንጂ፣ የሰም ዐብዮተኞች እለገበብ የዘረፏቸው ንብረትና ያወረሷቸው ድህነት፣ ብቻውን፣ ለማናደድ ይበቃ ነበር። ዘመድ አዝማድ እያጀበ ያሞቅ ያደምቀው የነበረ ያ ሙሉ ቤታቸው ተበትኖ ጭርታ ዋጠው። የቅጥር ሠራተኞቻቸው ሣይቀሩ፣ ነፃ ጉጆ ፍለጋ ተሠማርተው አልተመለሱም። ያልተለዩዋቸው ወደጆች ቢኖሩ፣ ታማኞቹ መንታ ድመቶቻቸው ነበሩ። በዚህ ሁኔታ ሲኖሩ ዐመታት አልፈዋል። በማንም የደረሰ ነው እያሉ፣ ያሉበትን ሁኔታ አያማርሩም።

በሩቅ ያሉ ልጆቻቸው ከየተሠማሩበት ጉራ አልፈው ደብዳቤ ይጽፉላቸዋል። ባንዳንዱ ደብዳቤ ውስጥ የሰፈረውን ሐሳብ ሲያነቡ፣ ልጆቻቸው እስከመጨረሻው ባይጽፉላቸው ይመርጣሉ። እጅግ መራራ ነው። ባላምባራስ አንድ ቀን በረንዳቸው ላይ ቁጭ ብለው፣ የማታ ፀሐይ ሲሞቁ፣ የድሮ የመንታ ልጆች ጎደኛ ሁለት ደብዳቤዎች አምጥቶ ይሰጣቸዋል። «ቤት ግባ» የማለቱ ልምድ ቀርቷልና «ደብዳቤዎቹ ከመጡ ሰንብተዋል በአደራ በሰው እጅ ነው የተላኩት። ሥራ በዝቶብኝ ትንሽ ዘግይተውብኛል!» ብሎ ነበር መልእክተኛው ለወንዱ ሰጥቷቸው ከደጅ የተመለሰው። ባላምባራስም ደብዳቤዎቹን ይዘው ባለቤት ትምክህተን እየጠሩ፣ «የልጆችሽ ደብዳቤ መጥተል! ቶሎ ነይ» ብለው ማርጀት ወደጀማመረው

አለ። ታዲያንን፣ የወንዱ አቅም ይህን ሁኔታ እንዴት ሊለውጠው ይችላል ብለሽ ነው፣ እንዳንቺ እንድጨነቅ የምትጋብዥኝ!» አሉ በተለመደ የዋይታ-ለበስ ሣቃቸውን፣ ገርበብ ባለ አፉቸው እየለቀቁት።

-«የፈሪዎች ቋንቋ ብዙና አወዛጋቢ ነው!» አሉ ትምክህተ፣ እንደመተቸት።

-«ይኸማ ለመሰው ወንዶች ተብሎላቸው የለ! በተለይ ያዲስ አበበውማ ወንድ ነገ ጃንሜዳ እንድትገኝ! ትገረፋለህ! 40-40 የሚል አዋጅ ቢወጣ፣ ገና ማለዳ ወፍ ሳይንጫጫ ተነስቶ፣ ራስ መኰንን ሲደርስ ልብሱን ማውለቅ ይጀምራል» እየተበለ ተተርቶበት የለ ብለው ወንዱ ይሥቃሉ።

-«አንተዬ! አሁን ያ መሩ፣ አለግባብ ስለተፈረደብን ጉዳይ ቢሰማ፣ እዚያው አለበት አምባ ተቃጥሎ አይሞትም!» በንዴት በጆቻቸው ያጨበጭባሉ።

-«ያርር እንጃ! እስቲ እንዴት ሁለቱንም ክስ በንዴ እናጣለን?» ይላሉ በለምበራስ ወንዱ፣ ባለፈው ሰሞን አለግባብ የተረቱበትን የቤት ክስ እያስታወሱ።

-«አንተዬ! እኔስ በጣም የገረመኝ፣ የባንኩንም ብድር እኛው እንድን ክፍል ሲወስኑ ነው። ቤቱ ተወርሷል። እንዴውም የሚኖርበት አንድ ከዲ ነው። ቤቱ ከተወረሰ የሚጠቀምበት ወራሹ፣ የባንኩንም ዕዳ መክፈል ሲገባው እንዴት እኛ እንከፍላለን። በመሠረቱ፣ ያንድን ቂሚ ቤት ፎቁን ብቻ ለይቶ ቢወርሰው ተገቢ አለነበረም። በርግጥ ግፍ ነው! ይህን ጉዳይ ያ መሩ ቢሰማ፣ እራስ ነብር ነበር የሚሆነው! አያስችለውም-ግፍ ሲፈፀም!» አሉ እናት ትምክህተ ኵለል እያለ የሚወርድ ድቡልቡል ዕንባቸውን ከፊታቸው ላይ በመዳፉቸው እየጠረጉ።

-«አንቺስ ያንገበገበሽ የባንኩ ብድር መክፈል ጉዳይ ነው! እኔን ግን እየቆጠቆጠ የሚያቃጥለኝ፣ በምኑም በምኑም ከኛ የማይሻል አንድ ጋጠ ወጥ «ከዲ» (ትምክህተ ከድሬውን እደምትጠራው) ከናታችን ላይ ተቀምጦ፣ ተፈናጦ፣ ማለት ይሻል ይሆን፣ ያገሩን ጋለሞታ ሁሉ በየምሽቱ እያፈራረቀ ዳንኪራ ሲረግጥብን፣ በየሰንበቱ የሚያርደውን ሙክት ፊርስ ሲጥልብን፤

በነጋ፣ በጠባ፣ ሲገባና ሲወጣ እየገለመጠ ሲያፌዝብን ማየቴ ነው።»

-«ድሮውንም ቢሆን፣ ሲያቀብጠን እንጂ፣ ይህን መሰይ ፎቅ መቼ ያስፈልገን ነበር?» አሉ ትምክህተ ውርደቱን ያመጣባቸው ፎቁ መሆኑን እያማረሩ። ሚዶ መስሏቸው ፀጉራቸው ላይ የሠኩትን ሹካ እየሰቁ በማንሰት። «ወይ ጉዴ ሹካውን ሚዶ አርጌዋለሁ ለካ!»

-«ፎቅ ቤቱንስ ምንም አልነበረ። የብሱን ሳለማጥበብና ለሌላውም ወገን እንዲደርሰው ስንል ነበር፣ ወደ ሕዋ የተስፋፋነው! እኔን የገረመኝ፣ እንድ ቁምን መኖሪያ ቤት፣ እንደትርፍ ቤት ተቆጥሮ ፎቁን መውረሳቸውና ለካዲ መስጠታቸው ነው!»

-«ምን አለፋህ ወንድዬ-ያ መሩ ይህንን በደለችንን ቢሰማ ኖሮ አያስችለውም! መራማ ሁልጊዜ የሚለው፣ ከሰው ጋር የመጣውን ሁሉ፣ እንዳመጣጡ መቀበል ነው። የኛን ማማ እሱ አለወቀ-እዚያሃች ተቀምጦስ እንዴት ሊያውቅልን ይችላል!»

-«መራንስ በእንድ ቁም ነገሩ አከብሬዋለሁ-ሀገር ተቆርሶ እንዳይሔድ ኬላውን በመጠበቁ!» አሉ በላምበራስ ሽከራ ግንባራቸውን እየሠነበሩ።

-« አይ ወንድዬ ቢቸግርህ ነው፣ ምኑን ይጠብቀዋል፣ ውስጣችን ተራቁቶ እርቃነ-ሥጋችንን ብቻ ቀርተን...» እንባቸው እንደተለመደው ከይኖቻቸው ምንጮች ይፈልቃል!

-« እዬ ትምክህተ-ያስችልሽ እንጂ - እኔ የሚገርመኝ እነዚህን ጥቁር ዓመታት ሁሉ ስታነቢ ዕንባሽ አለመድረቁ፣ ዐይንሽ አለማለቁ ብቻ ነው። ዕድሚያችንም ቢሆን ትንሽ አይደለም። ብዙ ዐይተናል። አላየሽም እንዴ ስንቱ ቀዘባ ወጣት በየፋፋው ወድቆ እንደቀረ? ተመስገን ማለት ነው!» አሉ ትምክህተን እያባበሉ።

-« በያድስን ነው እንጂ የምንጦርበት የዕረፍታችን ዘመን ነበር። እንደ ሌላውም ቤተሰብ የልጅ ልጅ ከበን፣ ዘመድ አዝማድ አጅበን የምንዝናናበት ወቅታችን ነበር። በመንታ ልጆቻችን ፈንታ፣ መንታ ድመቶችቻችን ብቻ ናቸው የቀሩን። በሩቅ የሚገኙ ልጆቻችንም ቢሆኑ ዐይጥና ድመት ሆነው፣ እንዴ ሌላውን ለማጥፋት እንደቋቱ ናቸው። የዘር ርግማን እንኳ ያለብን አይመስለኝም። ሁላችንም ወለጆቻችንን በሚገባ ጦረን ተዝናንተው ነው ያለፉት!

ዘወትር ብቻቸውን ሲሆኑ የተለመደች እንጉርጉሮአቸውን ያሰዝናሉ።

« የመንትዮች እናት ልቧም ሆኖ መንታ፣
ልብረር ልብረር ይላል፣ ወዳሉበት ቦታ፣
አንዱ ወደ ሰሜን፣ ሌላው ሰሜን ዋልታ፣
እንደፈረደበት ሔዶ ሲንገላታ፣
ባልፈጸመው ወንጀል፣ በልጆቹ ትዝታ!»

ወይዘሮ ትምክህተ ከጓዳ ይዘውት የመጡትን ጠርሙስ ከሳሎኑ ጠረጴዛ ላይ ያስቀምጡታል። ጠርሙሱ ጥቁር ስለነበረ ያረቄውን መጠን አያሳይም። ዕለቱን ለማዋል ያህል እንደሚበቃ ለመገመት፣ ትምክህተ ያመጡትን ጠርሙስ ያነቃንቃሉ።

-« ለዛሬ ይበቃሃል ወንድዬ-እኔ መቸም ብዙ እንደማልጠጣ ታውቃለህ...»አሉ፣ የቀረበው መጠጥ ብዙ እንዳልሆነ እየገለጹ ትምክህተ።

-« እሱስ ይበቃ ነበር! ግን ያመጣሽውን ጠርሙስ አይተሽል!» አሉ ወንዴ ውስጥ ውስጡን ሣቅ እፍኖአቸው።

-« ምኑን ይሆን ያመጣሁት? መቸም የኔ ቀልብ ጠፍተል»አሉ ትምክህተ ወደ ጠርሙሱ እየተመለከቱ።

-« የዘይት ጠርሙስ እንከ ቢሆን ይሻል ነበር! እኔ የገረመኝ የእደ ክሎኙ ጠርሙስ ከምግብ ቤቱ ክፍል መግበቱ ነው?» አሉ እየሣቁ ወንዴ!

-« ወይ እኔ በጠፋሁ! ለካስ ያመጣሁት እደክለኙን ኖርአል!» አሉ ትምክህተ ራሳቸውን በራሳቸው እየታዘቡ።

-« እዚያስ አልደርስም፣ በእትዬ አለች! ግን እንዴው ለመሆኑ የተሠቀለ ልብ የሚያወርዱበት መድኃኒት ሐኪሞች አይኖራቸው ይሆን? ብዙውን እየደበቅሁህ ነው እንጅ፣ በየቀኑ የማደርገውን ስሕተት ሰስታውስ፣ ነገሩ አለማረኝም!»አሉ እንደመተከዝ አንገታቸውን እቀርቅረው።

-« ውነትሽን ነው! ነገሩ አለማረኝም። አሁንስ የግድ መፍትሔ መፈለግ ከሚያስፈልገን ደረጃ ላይ ደርሰናል። መቸም ዋናውማ መድኃኒትሽ የልጆችሽ በአንድ ማዕከላዊ አቋም ላይ ተደራድረው

ቢተባበሩና እንደወትሮአቸው ቢፋቀሩ ነበር!...»አሉ ወንዴ እሳቸውም ተከዘው።

-« በእታ ካለች አንድ ቀን ያደርጉታል! በመሐሉ እኛ ተ ጉዳን እንጅ...»አሉ ትምክህተ በምኞት ሰመመን ተውጠው።

-« የኛን መ ጉዳት ተናገሪ እንጅ፣ እነሱስ የሕይወት ድብብቆሽ ጨዋታቸውን መቀጠላቸው የማይቀር ነው።

-«በምናምንበት እንሞታለን»፣ የሚሉ እምበሶችሽ አንዴ ሌለውን ካለጠፉ ሰላም የሚያገኙ አይመስለኝም። የማዝነው የነሱ ጦስ እኛን እንዲህ ቀልበ ቢስ ማድረጉ ነው»

-« ወንድዬ፣ ያን ያህል ሔደናል እንዴ?»አሉ ትምክህተ ተደናግጠው»

-« እንዴታ! ከዚህ የባሰ ምን ይመጣል?»አሉ ወንዴ ፈርጥመው።

-« ያደኰሎኙ ጠርሙስ ጉዳይ ነው እንዴ እንዲህ ያስመረረህ!»

-« ያደከሎኙ ጉዳይ ቀላል ነው። በዚያን ሰሞን የሆንሽው ግን ምንጊዜም ቢሆን ከኅሊናዬ አይወጣም!»እያሉ ማሰላሰል ጀመሩ።

-« የቱን ይሆን ወንድዬ?» በከረረ ጉጉት ጠየቋቸው።

-« ትምክህቴ ረስተሽው ይሆናል። በዚያ ሰሞን፣ መንፈቀ ሌሊት ላይ የሆንሽውን ዘወትር ሳስታውሰው ይዘገንነኛል። ድመቶቻችን ረስተን ባልዘጋነው የበስተግርጌ መስኮታችን በኩል ከመሹበት ሲገቡ፣ በቀሰቀሱን ጊዜ፤ እነመሩ መጡ ብለሽ በእንቅልፍ ልብሽ መንፈቀ ሌሊት ላይ መስኮቶቹን ሁሉ ከፍተሽ፣ ምግብ ለማምጣት ወደ ማዕድ ቤት ልትሔጂ ስትይ፣ አከላክዬ ያስቀረሁሽ ትዝ ይልሻል! በሌሊት ድንገት የሚነቁና ከልጋቸው ላይ ሰያውቁት ተነስተው፣ በያጋጣሚው የሞቱ ሰዎች ቁጥራቸው ጥቂት እንዳይመስልሽ ትምክህቴ...» አሉ ፈርጥመው።

-« እንደዚህ ካለውስ አደጋ ትጠብቀኛለች-በዓታ የት ሔዳ! ይልቅስ አሁን ከረቂው ፉት ፉት እንበልና፣ ደብዳቤዎቹን እናንብባቸው» ብለው፣ ከመጡት አረቂ በመለኪያ ይቀዱ ጀመረ።

-« እስቲ ቸር ያሰማን» ብለው የደብዳቤዎቹን ኤንቬሎፕ መክፈት ጀመሩ፣ የድርሻቸውን የመለኪያ አረቂ በንድ ትንፋሽ ከጨለጡ በኋላ።

ትምክህተ፣ ከረዥም እንቅልፍ የተቀሰቀሱ ይመስል፣ ሲያደምጡ ቆይተው፤

-« እኛ እንደሆነ ደንዝዘናል! መርደም ሆነ ልደት አይሰማንም። የሚያሰዝነን እርስበርሳችው የተጋደሉ መንቶች እየተበሉ መተረቻ መሆናቸው ነው»

«እንቺ ስለኛ መደንዘዝ ነው የምታስቢው። ልጆቻችን ግን በየግላቸው የሚያስቡት ስለወደፊቱ ትውልድ ደኅንነትና ብልጽግና ነው። ሁሉም እንደሚሉት፣ ትግላቸው ለጠቅላላው የሀገራችን ሕዝብ መድኅን ለመሆን ነው። ሞታቸውንም ቢሆን የሚቆጥሩት በመሥዋዕትነት ነው። የትኛው ወገን ትክክለኛ መስመር እንደያዘ ጊዜ ያሳያል። ለረጋውያኑ እኛ ግን የጠቀመን ፋይዳ የለም። ከዲው እናታችን ላይ ተቀምጦ፣ ይበልጥ እያስረጀን ነው፤ -እባክሽን አረቄውን ቅጂልኝ!» ይሉሉ ወንዴ።

-« ደብዳቤውን እንበህ ጨርስ ብዬ እኮ ነው» አሉና ትምክህተ አረቄውን ቀዱ።

-« እውነትሽን ነው! ለብ ከለኝ ወይ እቀንሰለሁ ወይ እጨምራለሁ! እዚያ ደረጃ ሳልደርስ፣ የመራን ደብዳቤ ለንብልሽ» እሉ እየቀለዱ።

ሚያዚያ 30/79/ዓም
ሁሌም በልቤ ላላችሁ ወላጆቼ፣
አባቴ ባላምባራስ ወንዴ
እናቴ ወ/ሮ ትምክህተ

የተለመደ ሰላምታዬን አቀርባለሁ።

የዐብዮት ግዴታ ሆኖብኝ በተሰጠኝ ኃላፊነት ሰበክን፣ ደብዳቤ ሳልጽፍላችሁ ዘገየሁ። ሆኖም ደኅንነታችሁን ከከባቢያችሁ ካሉ ካድሬዎች እሰማለሁ። መቸም ያ ወንበዴ እንደሚጽፍላችሁ አውቃለሁ። ባለፈው ወር ላይ ለጥቂት አመለጠ እንጅ ከዚህ የተላኩ የነበልባል አዞች ሊማርኩት ነበር። እንዲህ በሀገሩና በዐብዮቱ ላይ ወንብዶ አይቀራትም። አንድ ቀን ዋጋውን ያገኛል። አንድ ቀን ምርኮ ገብቶ፣ እንደተለመደው፣ የፍየል ወጠጤ ይዘየርበታል። አብዶ ይሆናል እንጅ፣ በርግጥ በጤናው፣ ሕዝቡንና ሀገሩን አይከዳም ነበር።

ያልተለመደ ድርጊት ተደናግጠው።

-«ትጠጣ እንደሆነ ልቅዳልህ! ድህነታችንን ሳይሆን ልጆቻችንን የሚያስረሳን ሌላ መፍትሔ ያለ አይመስለኝም!»አሉ ትምክህተ፣ እንደበታቸው በመጠጡ እንደመለፋደድ እየቃጣው።

-«ለጤናችን! እንኳን ከእንግዲህ ማለቱ አያዋጣም-ትምክህተ፣ ለሞታችን-ጽዋችንን እናንሳ!»ብለው፣ ያቺ ያረቄ ጠርሙስ ጠብታዋ እስከታላቅ ጠጥተው ዉረሱ። በስተምሽቱ ላይም፣ እንደምንም እየተንገዳገዱ፣ ተያይዘው አልጋቸው ላይ ወደቁ። መንቃታቸውን ያየ አንድም ሰው ባይኖርም፣ እንቅልፍ ሊወስዳቸው ገደማ፣ ባለምባራስ ወንዴ እንደ «ደህና አሰድረኝ ፀሎት»ያቺ የተለመደች እንጉርጉሮአቸውን ሲያሰዝኑ ይሰማ ነበር፣

-«የመንትዮች እናት ል ቧም ሆኖ መንታ፣
ልብረር ልብረር ይላል፣ ወደሉበት ቦታ፣
አንዱ ወደ ሰሜን፣ ሌላው ሰሜን ዋልታ፣
እንደፈረደበት ሔዶ ሊንገለታ፣
ባልፈጸመው ወንጀል፣ በልጆቹ ትዝታ!

«. . . መከረኛ እናት፣ መንታ ልጆቹ ወልዶ፣
አንዱ ሰት ሌላው ማይ፣ ጽናራን ዱብ ዕዳ፣
ወግ ደርሷት ሳትኖር፣ ባልሠራችው ፍዳ፣
ሳትኖር ልትሞት ነው፣ ህይወት ሆኗት በዳ . . .»

# የደረሱን መጻሕፍት መጽሔቶችና ጋዜጦች።

## መ ጻ ሕ ፍ ት

### ፩ ሀ/ የበሰለው ያራል

ከኃይሉ ገብረ ዮሐንስ (ገሞራው)
1980 ስዊድን
ዳግማዊ ኅትመት

ይህ መጽሐፍ የደራሲውን ምርጥ ምርጥ የሆኑ 12 ግጥሞች ይዟል። 224 ገጽ

### ለ/ በረከተ መርገም

ከኃይሉ ገብረ ዮሐንስ (ገሞራው)
1980 ስዊድን
ዳግማዊ ኅትመት

ይህ መጽሐፍ ብዙ ዝና ያተረፈውን የግጥም ሥነ ጽሑፍ ያቀርባል። የአዲስ አበባ ኮሌጆች አንድነት ማህበር በተቋቋመበት ዓመት (ማለት 1959 ዓ/ም) ለመጀመሪያ ጊዜ የሁሉም ኮሌጆች ተማሪዎች ለግጥም ውድድር በተሣተፉበት ጊዜ በተወዳዳሪነት ቀርቦ አቸናፊነት ያገኘ ግጥም ነው። የግጥሙ ርዕስ «በረከተ መርገም» ሲሆን እነሆ ከሃያ ዓመታት ያህል በኋላ የመጽሐፍ መልክ ይዞ ለአንባቢያን ቀርቧል። የዚህ ግጥም ታሪካዊነት የደራሲው የፍንዳታ ድርድሮች የመጀመሪያው ቁጥር መሆኑ ጭምር ነው። 96 ገጽ

ሐ/ ONENESS: POEMS IN MEMORY OF MOTHER AFRICA

1984 ስቶክሆልም ፣ ስዊድን
by Hailu

ይህ መጽሐፍ ስለአፍሪቃ በእንግሊዘኛ የተደረሱ አሥራ ሁለት ያህል ግጥሞች ይዟል። 88 ገጽ

መ/ CHINESE ENGLISH IDIOMATIC PHRASES

COMPILED BY HAILU
478 ገጽ

## ፱ ጉራማይሌ

ከዮናስ አድማሱ

ደራሲው ከ፲፱፻፷ ዓ/ም ጀምሮ በተለያየ ወቅት የጻፏቸውን ግጥሞች ይዟል። 54 ገጽ

## ፲ ሁሉም ሥራ ብዙ

ከደግ ካሣሁን

የአሜሪካንን ሀገር ባህልና የኢትዮጵያውያንን ባህል እያወዳደረ በሰሜን አሜሪካ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን በአዲሱ ባህል ወስጥ በመሥጠም ሂደት ላይ የሚያሳዩትን ጠባይ፣ የሚያጋጥማቸውን መደናገር በኩሸታዊ አቀራረብ ያቀርባል። 17 ገጽ

P.O. BOX 491226
College Park, Ga. 30349

፬ Preliminary Notes On Ethiopian History

Hailu Habtu 1987

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ፤

1/ The Historiography of Ethiopia
2/ The Geez script and the Book of Henock
3/ The Geez Bible
4/ Geez Numerals

የሚሉ አቢይ ምዕራፎችና ተቀጥለ ማብራሪያዎች ይገኛሉ። 43 ገጽ

፭ Transition and Development in the Horn of Africa

by Mulatu wubneh and Yohannis Abate

ይህ መጽሐፍ ኢትዮጵያ ከግዛታዊ ፊውዳል ሥርዓት ወደ መንግሥታዊ ሶሻሊዝም ያደረገችውን ጉዞ መተረክ ጀምሮ በሳቢያው የተከተሉትን የመንግስት ፖሊሲ፣ የኢኮኖሚ ዓለማ፣ የሕብረተሰብ ፕሮግራሞች፣ እንዲሁም በአለም አቀፍ ተዛምዶዋ ሀገሪቱ ያሳየቻቸውን ለውጦች ይዘረዝራል።

አብሮም ድርቅና ጠኔን፣ ትምህርትና የከተማ እድገትን የመሳሰሉትን በማብራራት መጽሐፉ ጥናቱን በሰፊው ያትታል። 224 ገጽ

፮ Peasants, Agrarian Socialism, and Rural Development in Ethiopia.

by Alemneh Dejene

ይህ መጽሐፍ ከመሬት አዋጁ ወዲህ በዚሁ ነጥብ ላይ በጥናት መልክ ከቀረቡት ጥቂት ጥናቶች አንዱ ነው። ጥናቱ የሚያተኩረው በአርሲ ክፍለ ሐገር ይሁን እንጂ የጥናቱ ውጤት ሌላውን ክፍል የሚመለከት ነው። ይህ ጥናት የተካሄደው አርሶ አደሮችን፣ የገበሬ ማህበር አባላትን፣ እንዲሁም የርሻ ወኪሎችን በመጠየቅ ነው። ጥናቱ ከሚያቀርባቸው መከራከሪያ ነጥቦች መካከል የገጠሬውን አራሽ ምርት ውጤት እንደያድግ መሠናከል የሆኑት ምክንያቶች የእርሻ ውጤቶች ዋጋ ማነስ፣ የፍጆታ እቃዎች እጥረትና የቴክኖሎጂ (ኪነ ጥበብ) መጓደል

(አለመሸሸል) ናቸው የሚል ይገኝበታል። የገጠሬዎችን ማህበር ወደጋርዮሽ የእርሻ ማህበር መቀየር ፓሊሲ የሚደገፉ እርሶ አደሮች ቁጥር ሩብ ያህል ብቻ እንደሆኑ ጥናቱ ይጠቅሰል። 162 ገጽ

፯ ፊተ ሚከኤል ሐሰማ ራከ፤ ዘ<u>ንታ ኤርትራ፣ ቃል ይሐልፍ ጽሑፍ ይተርፍ፤</u> ‘የከቲት 1986 ዓም

ይህ መጽሐፍ የኤርትራን ታሪክ ከጥንት ጀምሮ እስከሰንበት ዘመን ያትታል። ደራሲው ከዚህ ቀደም ተሟልቶ ያልተገኘውን ታሪክ ለማሟሳት ጥረት ማድረጋቸውን ይገልጹና የእያንዳንዱን ጎሣና ዓሴት ታሪክ ጥልቀት ባለው ሐተታ አቅርበዋል።

በእጅ የተፃፈ፣ አሥር ምዕራፍ፣ 236 ገጽ

## የፖለቲካ ጽሑፎችና ሠነዶች ፤

፩/ ከኢሕአፓ ድርጅት የደረሱን ፤

ሀ/«የአንድነት ግንባር ፖሊሲ »

ዲሞክራሲያ

ቅጽ 8 ቁጥር 5

ጥቅምት 20 ቀን 1974 ዓ/ም

9ገጾች

ጽሑፉ ኢትዮጵያ ወዴት፣ ኢትዮጵያ ምን ዓይነት አስተዳደር ያስፈልጋታል በሚሉ መሪ ጥያቄዎች ይጀምርና ለኢትዮጵያ ዲሞክራሲ ያስፈልጋታል በማለት ምላሽ ከሰጠ በኋላ በተለያዩ የሀገሪቱ ችግሮችና ጥያቄዎች ላይ አስተያየት እየሰጠ የኢሕአፖን አዲስ አቋም በማስመር ዲሞክራሲያዊ ግንባር ለዲሞክራሲያዊ ትግል ማስፈለጉን በማበከር ጥሪውን እያቀረበ ይደመድማል።

ዲሞክራሲያ

«የካቲት ግም ሲል»

ቅጽ 14 ቁጥር 1

የካቲት 1980

ይህ ቁጥር አብዮቱ ከፈነዳበት ከየካቲት 1966 ዓ/ም ጀምር ኢሕአፖ በአስራ አራት የካቲቶች ውስጥ ያደረገውን ትግል ፣ በዚሁ ወቅት የኢትዮጵያ አብዮት ያሰያቸውን ለውጦች በማተት የፀረ-ማዕከላዊው መንግሥታትና የፀረ-ሶቪየት ጣልቃ ገብነት ግንባር እንዲፈጥር ቅስቀሳ ያደርጋል።

8 ገጽ

<u>የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ የፖለቲካ ፕሮግራም</u>

መጋቢት 1976

የፕሮግራሙ አቢይ ነጥቦች ዘጠኝ ናቸው እነርሱም ፣

፩ ህዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ማቋቋም

፪ ሰፊ ዲሞክራሲያዊ የሆነ የፖለቲካ መሠረት መጣል

፫ ብሔራዊ ኢኮኖሚ መገንባት

፬ የብሔሮች/ብሔረሰቦችን የራስ እድል በራስ የመወሰን መብት ማክበርና ማስጠበቅ

፭ የሠራተኛውን ህዝብ መብትና ጥቅም ማስጠበቅ

፮ ህዝባዊና ዲሞክራሲያዊ ባህል፣ የትምህርት ሥርዓት፣ ሰፊውን ህዝብ የሚያገለግል የጤና ጥበቃ ሥርዓት መገንባት

፯ የሰፊውን ህዝብ መብት፣ ፍላጎትና ጥቅም የሚጠብቅ የጦር ኃይል መገንባት

፰ በወንዶችና በሴቶች መሀል የእኩልነት መብት ማስከበር

፱ በገለልተኛነት ፣ በሰላም ፈላጊነት በፀረ-ኢምፔሪያሊስት ላይ የተመሠረተ ፖሊሲ መከተል

30 ገጽ

<u>እድማስ</u>

ቅጽ ፩ ቁጥር ፩

በሰሜን አሜሪካ የኢሕአፓ ኮሚቴ «ኢትዮጵያን በሚመለከት ፖለቲካዊ፣ ወታደራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ባሕላዊና ማሕበራዊ ጉዳዮች ላይ...» የሚያተኩር የመጀመሪያውን ቁጥር አውጥቷል።

<u>እድማስ</u>

ቅጽ ፩ ቁጥር ፪

«የደርግ ፀረ አንድነት ኢትዮጵያ ከተት» በሚል ርዕስ እንቀጽ ይጀምራል የተለያዩ የፓርቲው ዜናዎችና የዜና ትንተናዎችን ያቀርባል።

16 ገጽ

፬ DEMOCRATIC FRONT FOR THE LIBERATION OF ETHIOPIA

Political Programme

November 21, 1981

ዘጠኝ አንቀጾች የያዘ ባለ 12 ገጽ የፖለቲካ መመሪያ ነው።

የፖለቲካ መመሪያዎች በጭሩ፣

ሀ/ "ፋሺስቱን" መንግስትና የሶቪዬት ኢምፔሪያሊዝምን ደምስሶ በቦታው ነፃ ሪፐብሊክ መመሥረት፤

ለ/ ሰፊና ነፃ ዲሞክራሲያዊ የፖለቲካ ሥርዓት ማቋቋም፤

መ/ የሕዝቡን ኑሮ ለማሻሻል ከውጭ ተጽዕኖ የነፃና ዲሞክራሲያዊ ብሔራዊ ኢኮኖሚ መገንባት።

ሰ/ በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ብሔሮችና ብሔረሰቦችን እኩልነት ማወቅ፤ የብሔሮችንና ብሔረሰቦችን የራስን እድል የመወሰን መብት ማወቅ።

ረ/ የሕዝቡን ጥቅምና ፍላጎት መጠበቅ። ዲሞክራሲያዊ መብታቸውን ማስከበር።

ቀ/ ሀገራዊና ዲሞክራሲያዊ ባህል መገንባት ትምህርት ለሁሉም እንዲደረስ ማድረግ ፣ ሕዝቡ የሚገለገልበት የጤና ጥበቃ ሥርዓት ማቋቋም።

በ/ ኢትዮጵያን ከውጭ ወረራ ለመከላከልና የሐዝቡን ጥቅምና ፍላጎት ለማስከበር ብሔራዊ ጦር መገንባት።

ተ/ የፃታዎችን እኩልነት መጠበቅ። በሀገሪቱ ኋላቀርነት በባህሉ ኢኮኖሚና ፖለቲካው ደረጃ ምክንያት በሴቶች ላይ የደረሰውን ጭቆና ማስወገድ።

ቸ/ በሰላም አብሮ በመኖርና በነፃነት መርሆ ላይ የተመሠረተ የውጭ ሀገሮች ግንኙነት መመሪያን መከተል። የተባበሩት መንግስታትና የአፍሪቃን አንድነት ድርጅት ሠነዶች ማክበር። የአፍሪቃ ሕዝቦች ለነፃነት የሚያደርጉትን ትግል መደገፍ።

፫ ከመ.ኢ.ሰ.ን የደረሱን

ሀ/ <u>ሰአዲሲቱ ኢትዮጵያ</u>
ህዳር/ታህሳስ 1980
3ኛ ዓመት ቁጥር 15

ለ/ <u>ሰአዲሲቱ ኢትዮጵያ</u>
መጋቢት/ሚያዚያ 1980
4ኛ ዓመት ቁጥር 16
ርዕሰ አንቀጽ ፤ «በአንድነት ስም ፀረ አንድነት»

ሐ/ <u>ቀይ አድማስ፣ RED HORIZON</u>

ቅጽ 8 ቁጥር 51/2
የመሰ ኢትዮጵያ ኮሙኒስት ሊግ ልሳን
ሰሺሊስት ኢንተርናሽናል የተባለ ድረጅት (የስዊድን ቅርንጫፍ) በ3ኛው ዓለም ያሉ ማናቸውም ድርጅቶች ድርጅቱ ያሰፈራቸውን 4ነጥቦች አሟልቶ ከተገኘ እስከ 50,000 የስዊድን ክሮና እንደሚሰጥ ይጠቅሳል።

፬ ከሕዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ ድርጅት

ሀ/ <u>የትግል ጥሪ</u>
3ኛ ዓመት ቁጥር 11
በህዳር/ታህሳስ 1980 ዓ/ም
በመጽሔቱ ወስጥ የተብራሩ ርዕሶች
1/ የህወሓትና የመኢሰን የጋራ መግለጫ
2/ የከፋ ረሀብ እንደገና
3/ ታጋይ ክንዶች ሲተባበሩ
4/ እብሪተኛው የብሔራዊ ጭቆና አዋጅ
74 ገጽ

ለ/ ወጣ ወጣና እንደሸንበቆ ተንከባለለ እንደሙቀጫ የኢሕአፓ ትራጀዲ

ግሊሊት 1979 ዓ/ም

በአራት አቢይ ክፍሎች የተከፈለ በኢሕአፓ ድረጅት ላይ በተለያዩ የፖለቲካ ነጥቦች ላይ ግሊሊት ያቀረበውን ሂሰዊ ትችት ይዟል።

341 ገጽ

ሐ/ የኤርትራ ህዝብ ትግል፣ ከየት ወዴት (ግምገማ)

ሀወሐት 1979 ዓ/ም

ይህ በሰባት አቢይ ክፍሎች የተጠቃለለ መጽሐፍ ሰፋ ባለ አቀራረብ የኤርትራ ህዝብ ትግል ፣ ሀወሐት ከኤርትራ ግንባሮች ጋር ስለነበረውና ስላለው ግንኙነት ዓይነት ይዘረዝራል። 33 ገጽ

መ/ የትግል ጥሪ

3ኛ ዓመት ቁጥር 12

ጥር/የካቲት 1980 ዓ/ም

በዚህ ልዩ እትም ውስጥ ሀ/ የወቅቱ ሁኔታና የኢትዮጵያ አንድነት ጉዳይ ለ/ የኢትዮጵያ ዲሞክራቶች የወቅቱ አጣዳፊ ተግባር የሚሉ አቢይ ርዕሶች ቀርበዋል።

62 ገጽ

ሠ/ PEOPLE'S VOICE

January 1988

ይህ እትም የተለያዩ ዜናወችና ትንተና ይዞ ቀርቧል።

24 ገጽ

ረ/ «በድርቅና በረሃብ የተጠቃውን ሕዝብ አስመልክቶ የተሰጠ መግለጫ»

ይህ ጽሑፍ ጦርነቶች እየተፋፋሙ በሉበት ሁኔታ የረሀብ ችግርም እየተባባሰ መምጣቱን መነሻ በማድረግ ለችግሮች መፍትሄ የሚሆኑትን ዘዴዎች በመጠቆም ይጠርሳል።

3 ገጽ

ሸ/ ኢትዮጵያ ወዴት? እንዴት?

የኢትዮጵያ አርሶ አደር በፖለቲካ ባርነት ስር ይገኛል።

በዚህ ጽሑፍ ህወሓት በተለያዩ የአርሶ አደሩንና የኢትዮጵያን አብዮት በሚመለከቱ ነጥቦች ላይ ያለውን አመለካከትና ሌሎች ቡድኖችና ግለሰቦች ከሚሉት አንፃር የሚለይበትን ነጥብ ይጠቅሳል። የጽሑፉ ማዕከላዊ ነጥብ የአርሶ አደሩ ጥቅምና ፍላጎት እንዳይሟላ ገደብ የጣሉበት ደርግና የሶቪየት ጣልቃ ገብነት ነው የሚል ነው። ከዚህ ተነስቶ ጽሑፉ እነዚህ ስርአቶች መደምሰስ አለባቸው ሲል ይደመድማል።

፳ ሞረሽ

«ተግባር ይናገር»

ቅጽ 1ቁጥር 3

ጥር 1980 ዓ/ም

ይህ ቁጥር የሚያትተው የህብረት ግንባር መገንባት እንደሚቻል ሲሆን፣ «የሁለትዮሽ ግንኙነት» ንድፈ-ሀሳቡን በማብራራት ፀረ-ደርግ ፣ ፀረ-ሶቪዬት ግንባር ለመመሥረትና ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመፍጠር የሚያስችለውን መንገድ ይጠቁማል።

8 ገጽ

፯ ህ.ግ.ሐ.ኤና ህ.ወ.ሓ.ት

## የህ.ግ.ሐ.ኤና የህ.ወ.ሓ.ት የጋራ መግለጫ
## ናይ ህ.ግ.ሐ.ኤን ናይ ህ.ወ.ሓ.ትን ሓበራዊ መግለጺ
## E.P.L.F/T.P.L.F JOINT STATEMENT

ይህ የጋራ መግለጫ «የኤርትራ ሕዝብ ፀረ ቅኝ አገዛዝ ትግል ወደ መጨረሻ ድሉ የተቃረበበት «እንዲሁም የኢትዮጵያ ሕዝቦች ... ለዘመናት ሲያሰቃያቸው የቆየውን ፀረ ሕዝብ ስርዓት በተባበረ ትግላቸው ደምስሰው በመፈቃቀድና በእኩልነት ላይ የተመሠረተ ዲሞክራሲያዊ ስርዓት የሚገነቡበት ቀን እየተቃረበ በመሄድ ላይ ነው « በሚሉ መነሻ ሐተታዎች ይጀምራል።

ባለፉት ጥቂት ወራት ህዝባዊ ግንባር ሓርነት ኤርትራ (ህ.ግ.ሐ.ኤ) በኢ.ሰ.ፓ ላይ ችንፈት ማድረሳቸውን መግለጫው ይጠቅስና ሁለቱንም ድርጅቶች አዲሱን ሁኔታ በመገምገም ተቋርጦ የነበረውን ግንኙነት ለማደስና ለመደጋገፍ በፖለቲካ ጽሕፈት ቤት ደረጃ የአምስት ቀናት ግንኙነት ማድረጋቸውን ይገልጻል። ሁለቱም ድርጅቶች በጋራ ለመስራትና ለመደጋገፍ የሚያስችሏቸውን አምስት ነጥቦች አስቀምጠው ኢ.ሰ.ፓ ያወጀውን «የእልቂት አዋጅ» ለመመከትና ለማክሸፍ ለኤርትራና ለኢትዮጵያ ሕዝቦች ቃል ሲገቡ የኢትዮጵያና የኤርትራ ታጋይ ድርጅቶች ለዚሁ ተግባር እንዲተባበሩ ጥሪ ያደርጋሉ።

፯ <u>ከግለሰቦች የደረሱን፤</u>

ሀ) ግለሲት ዘለሊ
«ፀቢብ ብሄራዊነት ዘግስዮ ቃልስና» ቁ. 1
ካብ በሪሁ
ሰ ኤ፣ 1980
በትግርኛ የተደረሰ

ይህ ጽሑፍ ዓላማ አድርጎ የተነሳው በትግራይ ህዝብ የሚካሄደውን ብሄራዊ ትግል በመገምገም ጉድለቶች በሕብረት የሚስተካከሉበትን መንገድ ለመሸት ነው። ጽሑፉ ግሌሊትን በመንቀፍ ያተኮረ ነው።

የጽሑፉ ይዘት፤
መእተዊ ቃልስና
ስንኩል ግ ኒፈስቶ -68
ኣብ መደብን ፖሊሲ ምውጣጥ
ድሕሪ 2ይ ጉባኤውን ጽበት
ግሌሲት ዘለሊ
27 ገጽ

## ነፃ መጽሔቶችና ጋዜጦች

፩-ሀ ሕብረት፤

እትም ፩ ቁጥር ፪

ይህ መጽሔት በርዕሰ አንቀጹ «ረሀብ እንደገና በኢትዮጵያ» በሚል ርዕስ ለረሀቡ መንስኤ ተፈጥሮ ብቻ ሣይሆን ጦርነትና ሰው ሠራሽ ችግሮች ለሕዝቡ አለቂት ተጨማሪ ምክያቶች መሆናቸውን ይጠቅሳል።

እንዲሁም የተለያዩ ዜናዎች፣ የስልክ ማውጫዎች፣ ልዩ ልዩ ሥነ ጽሑፎች፣ የንግድ ማስታዎቂያችና ለኢትዮጵያውያን ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎችን ይዞ ቀርቧል።

27 ገጽ

ለ- ሕብረት፤

መስከረም ፲፱፻፹፩ ዓም /September 1988/

መጽሔቱ በርዕሰ አንቀጹ በመላው ዓለም የሚገኙ የኢትዮጵያ ስደተኞች የሚደርስባቸውን ችግር በመዘርዘር ይህን ችግር ለመቋቋም «የኢትዮጵያ ስደተኞች ዓለም አቀፍ ድርጅት ያስፈልጋል» በማለት ጥሪ ያደርጋል። እንዲሁም ምርምርና ጥናት፣ ከኪነት ዓለምና ስፖርት ዓምዶች ላይ አንዳንድ ኢትዮጵያውያን በቴክኖሎጂ፣ በፊልም ሥራ፣ በድራማ፣ በስፖርትና በንግድ ተሠማርተው ያበረከቱትን ውጤት ያስተዋውቃል። ይህ እትም ልዩ ልዩ ዜናዎች፣ ግጥሞች ይዟል።

Hibret
P.O. Box 2457
San Jose CA. 95109

፱ የኢትዮጵያ የአፍሪቃ ጥናት መጽሔት በተለይ በአፍሪቃ ቀንድ ላይ የሚያተኩር/ Ethiopian Journal of African Studies with Special Emphasis on the Horn of Africa

Vol.4 No.2

September 1978

Asmara University-Institute of African Studies

81 ገጽ

፲ ጣፍ

ቅጽ 2 ቁር 1

ማርች 30 ቀን 1988

ሎስ አንጀለስ ከሊፎርኒያ በየስት ወር የሚታተም የአማርኛ ሥነ ጽሑፍ መጽሔት። ይህ ቁጥር በስደ ነባብና በግጥም የተደረሱ ስነ ጽሑፎችን እንዲሁም ተረትና ምሣሌ ይዞ ቀርቧል።

፲፩ FRIENDS OF ETHIOPIA NEWSLETTER

No. 7 1988

Friends of Ethiopia

P.O. Box 42533

Washington DC 20015-0533

ይህ ጋዜጣ ኢትዮጵያን በሚያውቁና ኢትዮጵያን በሚወዱ አሜሪካውያን የሚዘጋጅ ነው።

፲፪ መስታዎት

በካሊፎርኒያ የሚታተም የአማርኛ መጽሔት ሲሆን የመጀመሪያ ቁጥሩ የተለያዩ ዜናዎች ፣ ትችቶችና ማስታወቂያዎችን ይዞ ወጥቷል።

፮ <u>1988 ETHIOPIAN BUSINESS DIRECTORY</u>

With an Information Guide to the Washington Metropoliitan Area.

Ethiopian Community Development Council, Inc.

ይህ ጥራዝ በዋሽንግተን ዲሲና አከባቢው ያሉትን ቁልፍ ቦታዎችንና የኢትዮጵያውያን ሙያተኞችን እንዲሁም የንግድ ተቋሞችን አድራሻ የያዘ መመሪያ ነው።

76 ገጽ

፯ <u>Proceedings 2nd International Conference on the Horn of Africa</u>

«The Ethiopian Revolution and Its Impact on the Politics of the Horn of Africa»

May 29-30, 1987 New York

ይህ ጥራዝ በጉባኤው ላይ ቀርበው የነበሩትን የአስራ ሶስት ተሣታፊዎችን ወረቀቶች መዝገብ አውጥቷል። የዚህ ጥራዝ ዋና ትኩረት በኢትዮጵያ አብዮት ላይ ሲሆን ፣ ኢትዮጵያውያን በብዛት የተሣተፉበትና በብዛት ወረቀት ያቀረቡበት ጥራዝ ነው።

# ቅ ኔ

ለ ጽሁፌ መጀመሪያ ይሆነኝ ዘንድ ስለ አንድ የመጠጥ ቤት ቅኔ አመራመር ለቅርብ ፦

አለተ ቅዳሜ ማታ ከሠኞ እስከ ቅዳሜ ቀትር በሥራ ላይ የዋለን ዓይምሮ በመጠጥ ለማዝናናት የእመት አትለፉኝ ጠላ ቤት ከሠኞ እስከ አርብ ካሉት ማታዎች የበለጠ ተጨናንቋል።
እመት አትለፉኝ ከገንዘብ ማስቀመጫው ጐን ቁጭ ብለው ጠላቸውን ይቀመቅማሉ። ታዲያ እመት አትለፉኝ የማይወዱት አራስ በርሀ (መለጣ) ሲገባ አይተው እሱን ለማናደድ ሲሉ በቅኔ እንዲህ ሲሉ ተናገሩ።

ትሰሙኝ እንደሆን ልንገራችሁ በውነት
በራሠው እንጀት ነው ቅቤውን መጠጣት።

ገፄከ መምጣቱ በቅኔ የተዘለፈው በርሀ መለጣ ሁለት ብርጭቆ ጠላ በቁሙ ጨልጦ እንዲህ ብሎ መለሰ

በናርኩበት ሁሉ ባለፍኩበት ዘመኔ
እንደች ያለ በጥባጭ አላየሁም እኔ።

በዚህ ሠው አነጋገር የተናደዱት ወ/ሮ አትለፉኝ እንደጠሉት ሲነግሩት

ይህን ሁላ ጠላ የበጠበጥኩት
ላንድ ጋን ላጠጣ መቸ እኔ አሰብኩት።

ይሉቷል። ይሄን ጊዜ ጠላውን ያልወደደው መሆኑን እንዲህ ብሎ ተናገረ።

ምንም ድሀ ብሆን ባይኖረኝም ተድላ
ሰጠጅ ነው እንጂ አልጊጊም ሰጠላ።

ይላል። የእመት አትለፉኝ ደንበኛ የሆኑት ሸበቶ በመሀል ገብተው እንዲህ ሲሉ ጨሬውን ወደ ጥሩ ለወጡት፣

ጠላውን በጥብጠሽ እሱ ከጠላው
ትመቻለሽ አንቺ ከዚህ ሁሉ ሰው።

እመት አትለፉኝ ስለተሞገሱ ደስ ብሏቸው እንዲህ ሲሉ መለሱ

ድሮም እድሌ ነው ኗሙ የሸበተ
እንደ መንፈቅ ህፃን እርጎ እንደተጋተ።

ይሏቸዋል። ይህን ጊዜ ወጣጡ (በርሃ) ጥልቅ ብሎ፣

ድሮም ለጠላ እርጎ ነው እርካሹ
እንደዚህ ያሉትስ ጥሩ ነው ቢያመሹ

ብሎ የጠጣበትን ከፍሎ አትለፉኝ ጠላ ቤትን ጥሎ ወጣ

Mr. Pen
ከ ኒውጀርሲ፤ ሰሜን አሜሪካ

# የ ቃ ለ ት ፍ ች

ከዚህ በታች የቀረቡት ፍችዎች የተገኙት ከሚቀጥሉት ምንጮች ነው፤

1/ ከዶክተር አምሳሉ አክሊሉ፤ የውጭ ቋንቋ ጽንሰ ሐሳብ ትርጉም በአማርኛ
2/ በኢትዮጵያውያን የዩኒቨርሲቲ መምህራን የውይይት ማህበር የተዘጋጀ፤ ተራማጅ መዝገበ ቃላት /የጽንሰ-ሀሳብ ቃላት መፍቻ፤
3/ Academy of Ethiopian Languages; English-Amharic Glossary of scientific and Technical Terms
4/አቶ ተክለማሪያም ሀይሌ፤ የአገር በህልና ስልጣኔ አያያዝ፣ ፲፱፺፱ ዓ.ም

| | |
|---|---|
| Anti- | ፀረ፣2 ተቃራኒ፣ የማይስማማ1 |
| Counter | ፀረ 1 |
| Co | አበር1 |
| Pre | ቅድመ ፣ ከ...በፊት፤1 |
| inter | አብሮ መስራት/መደረግ1 |
| semi | ከፊል 1 |
| sub | ንኡስ፣ ታች1 |
| ex | ያለፈ፣ ወጥ፣1 |
| extra | ተጨማሪ፣ልዩ፤1 |
| inter | በመሀል፣ ከ...ጋር፣ |
| | እርስ በርስ፤1 |
| mal | ትክክል ያልሆነ፣ መጥፎ፣ |
| | ቅንነት የሌለው ፤1 |
| mis | አፍራሽ፣ ግማሽ፤1 |
| mid | አጋማሽ፣ ግማሽ፤1 |
| pro | ደጋፊ 1 |
| re | እንደገና 1 |
| semi | በከፊል፣ መሰል፤1 |

| | |
|---|---|
| sub | ንዑስ፣ ታች፣ -ሥር፤1 |
| super | ላይ፣ ከፍታ፤1 |
| trans | አቋራጭ፣ መስወጥ |
| un | አፍራሽ፣ ያል-፣ የም-፤1 |
| opposition | ተቃውሞ 1 |
| principle | መሠረተ ሐሳብ፤ መርህ፤2 |
| problem | ስያስ፣ ችግር፣ ጣጣ፤4 |
| politics | ፖለቲክ፣ ሀይለ መንግስት፣ |
| | ስነ መንግስት፤ |
| | ህብረ መንግስት፣ አውደ መንግስት፤4 |
| perception | ህዋሳታዊነት፣ ውስጠ ህሊና4 |
| percepetual | ህዋሳታዊ2 |
| spontaneous | ግብታዊ |
| spontneity | ግብታዊነት 2,4 |
| structure | መዋቅር 2,4 |
| strategy | አዘግመት፣ አወጋግ፣ |
| | ሀይለ ፍልሚያ4 |
| surplus value | ድርብ ድርብርብ ትርፍ 4 |
| tactic | ስልት፣ አሰላለፍ፣ ዘዴ፣ ጊዲራ4 |

## ለሥነ ጥበብና ኪነጥበብ የሚጠቅሙ ቃላት 3

| | |
|---|---|
| Artery | ደም ወሳጅ |
| Back bone | አምደ አጽም |
| Bisexual | ወንዳገረድ |
| Canine | ክራንቻ |
| Cataract | ሀበላ (ትግርኛ) |
| Cone | ልቃቂት |
| Constipation | ሆድ ድርቀት |
| Contraceptive | ከላኢ ወላዲ |

| | |
|---|---|
| Copulation | ሩካቤ |
| Cross Fertilization | ጣምራዊ ጽንስ |
| Cycle | ዑደት |
| Digestion | ልመት |
| Egg Shell | የእንቁላል ቅርፊት |
| Fertilization | ጽንሰት |
| Gland | እመጪጢ /እመንጪ እጢ/ |
| Hematology | ሥነ ደም |
| Hermaphrodite | ወንዳገረድ |
| Insemination | ግብእተፍስ |
| Menopause | እርጠት |
| | |
| Boulder | ቋጥኝ |
| Brass | ነሐስ |
| Carbonation | ቅሬተ-ካርበን |
| Cave | ዋሻ |
| Celestial | ጠፈራማ |
| Caldera | ሰፋ፣ ሰርጓዳ መሬት |
| Basin | ትልቅ ዝብጥ |
| Basalt | ባርያ ድንጋይ |
| Axis | ምሕዋር |
| | |
| Anti matter | ፀረ ቁስ |
| Apex | አናት |
| Area | ስፋት |
| Arrow | ፍሊጣ |
| Astronautics | ስነበረራ ጠረፍ |
| Astronomy | ስነሁለንታ |
| Attraction | ስበት |
| Beam | አመልማሎ |

| | |
|---|---|
| Probability | ይሆንታ |
| proof | አርግጦሽ |
| proportion | ምጥነት |
| Random sample | ነሲብ ናሙና |
| Range | ርቀት |
| Ratio | ሚዛን |
| Raw Data | ጥሬ ውሀብ |
| Response | ክትለት |
| Sequence | ድርድር |
| Skewness | ዝመት |
| Statistic | ሥልጠት |
| Statistics | ሥነ ሥልጠት |
| Stochastic Model | ይሆንታ ምስለት |
| Stratification | ሽንሸና |
| Table | ሰንጠረዥ |
| Tabulate | ሰንጠሬ |
| Tabulation | መሰንጠር |
| Variable | ተለዋዋጭ |
| | |
| Current | ከረንቲ |
| Conduit | ችቦ አቃፊ |
| Component | ምንዝር |
| Conduction | ግብነት |
| Diagram | መጽሐት |
| Dissipate | ማባከን |
| Distortion | ዝንፈት |
| Efficiency | አሳባ |
| Electromagnet | ኤሌክ መግነጢስ |
| Generator | ሠራጊ ኃይል |

